ፓኖራማ ቁጥር 92

ሐምሌ 6 ቀን 2002 ዓም

# የትዝብት አድማስ

## ጠላትህን በሚገባ ካወቅኸው

## ልትጠቃ አትችልም

" በቅድሚያ ራስህንና ጠላትህን በሚገባ እወቅ፥ ከዚያ በኋላ

ሳትቸነፍ መቶ ጦርነቶችን መዋጋት ትችላለህ "

ሰን ዙ Sun Tzu

ይህንን ጥቅስ የተናገረው በአራት መቶ አመተ- ዓለም አካባቢ የነበረ የቻይና የጦር ስልትና ስትራተጂ አዋቂ ነበር ።

ጠላቱን በሚገባ ያላወቀ የጦር መሪም ይሁን ሕዝብ ዘለዓለም ከችንፈትና ከጥቃት ከውርደትና ከጭቆና ፥ ከመገዛትና ከመነዳት ሊያመልጥ እንደማይችል ፥ ይህ ሰው ፥ የጦርነት ጥበብ በተሰኘው መጽሐፉ በዝርዝር ተንትኖታል ።

ለአለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በምኒልክ ግቢ መሽጎ የተቀመጠውን ብሄረተኛ ቡድን፥ ማንነቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ገና አልታወቀም ለማለት ቢከብድም ፥ ተቃዋሚ ነኝ የሚለው ክፍል ሁሉ ግን የዚህን ዘረኛ ሥርዓት አራማጅ ግለሰቦችን ዕውነተኛ ባኅርይና ሰብዕና በሚገባ አውቋል ለማለት የሚቻል አይሆንም ። ያማ ባይሆን ኖሮ ፥ በተደጋጋሚ የነ መለስ ዜናዊ መጫወቻ ለመሆን ባልበቃ ነበር ። ያማ ባይሆን ኖሮ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ ለወያኔ ጥቃትና ውርደት አይጋለጥም ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ ተቃዋሚ

ነን ያሉትን ክፍሎች ተቀብሎ በማስተናገድ፥ ከወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ነፃ ያወጡኛል ብሎ ድጋፉን አልነፈጋቸውም ነበር ። እነርሱ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ወያኔን የሚያወቀውን ያህል ባለማወቃቸው ፥ እንኳንስ ሕዝቡን ነፃ ሊያወጡ ቀርቶ ፥ እራሳቸውንም ቢሆን ከውርደትና ከሽንፈት ነፃ ሊያወጡ አልቻሉም። ይህም በመሆኑ፥የኢትዮጵያ ሕዝብ በነርሱ ላይ የነበረውም ዕምነትና ተስፋ እንደጉም ተነነኖ ቀረ ። ያለ አይዞህ ባይና ያለ መከታ አስቀሩት። የተከፈለው መሥዋዕትም ለጊዜውም ቢሆን መና እንደሆነ አስቆጠሩት ። ታዲያ ዛሬ ለጊዜውም ቢሆን ወያኔና ግብረ አበሮቹ ኀይላ እየደነከሩ ናቸው።

በጦርነት ታሪክ ሂደት፥መቸነፍና ማቸነፍ፥መግደልና መሞት፥ መማረክና ማምለጥ፥ የነበረ፥ ያለ ፥ወደ ፊትም የሚኖር መሆኑ ቢታወቅም ፥ የአመኑትን መክዳትና ለጠላት አሳልፎ መስጠት ግን ሞት ብቻ ሳይሆን የሞትም ሞት ነው ። የሞት ሞት የሚመጣው ደግሞ መጀመሪያውኑም ቢሆን የሚገጥሙትን ጠላት ጠንቅቆ ካለማወቅ የመነጨ ድንቁርና ወይም ንዝህላልነት ፥ ካልሆነ ደግሞ ፍርሀትና ጥቅመኝነት ነው። በመሳሪያ ብዛት፥ጥራትና ዓይነት፥ በሠራዊት ሥልጠናም የተዘጋጀ ብቻ ሳይሆን ፥ የውጊያ ችሎታ የነበረውን፥ ግዙፍ ጦር የመሩት የደርግ ባለሥልጣናት ፥ የወያኔን ማንነት በሚገባ ባለማወቃቸው የሀገሪቱን የመከላከያ ኃይል ያለ መሪ ለጠላት አጋለጡት ። ለውርደት ዳረጉት ። ሀገሪቱንም ለበላዒ-ሰብ አስረክበዋት ሄዱ ። ጠላትን በሚገባ አለማወቅ ዘለዓለም የጥቃት ሰለባ ሆኖ መቅረት ነው ። ይህ ሃቅ በጦርነት ብቻ ሳይሆን በፖለቲካውም መድረክ ጭምር ተከስቷል ። አሁን ታዲያ የሚያስፈልገው ባለፈው ችግራችን ላይ መብተክተክ ሳይሆን፥ ያ ስህትት እንዳይደግም ተጠንቅቆና ተግቶ መሥራት ብቻ ነው ።

ለአለፉት ሃያ ዓመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልካዓ- ምድር በአመዛኙ ሰፍኖ የነበረው ክስተት ተቃዋሚው ክፍል በራሱ አነሳሽነት፥ የትግል ዕቅድና ርምጃ በመነሳሳት ወያኔን መጋፈጥና ማስጨነቅ ሳይሆን፥ በወያኔ ድርጊትና ርምጃ ላይ ምላሽ በመስጣት ላይ ብቻ ያተኮረ ለመሆኑ ማንም ሰው ሊያስተባብለው የሚችል አይደለም ። በተለይማ የወያኔን መንግሥትነት ተቀብለናል በማለት፥ የመለስ ታማኝ ተቀዋሚ ተብለው የተፈረጁት ክፍሎች ጊዚያቸውን ያባከኑት ለመለስ ዜናዊ አጀንዳ ምላሽ በመስጠት ላይ ብቻ ነበር ። በቀደደላቸው ቦይ ፈሰዋል።ሲቃኛቸው ተቃኝተውለታል። በመለስ ዜናዊ ሙዚቃ ደንሰዋል። በአምባገነኖች ሥርዓት በተዘጋጀ ድግስ ገብቶ መደንከር ፥ ሕዝባዊነት አይደልም ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ጥቅም ቆመያለሁ ብሎ የሚታገለው ኃይል ይህንን ድርጊት ያወግዘዋል። ራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብም ቢሆን የሚንቀው ፥ የሚጠላውና የሚያወግዘው መሆኑን በአለፈው ግንቦት ወር 2002 ዓም በተግባር ገልጾታል።

በሀገር ቤት ባቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ጭምር የታወቀውን የወያኔን ወንጀል፥ እናጋልጣለን ብሎ መዳከር ፥ ቢያንስ የዋህነት ያለዚያ ደግሞ ለመለስ ዜናዊ የንግድ ማስታወቂያ ሥራ ከመፈፀም አያልፍም ። እረ ለመሆኑ ወያኔዎቹ እራሳቸው ሳይፈሩና፥ ሳያፍሩ፥ የታሪክም ሆነ የህግ፥ የኀሊናም ሆነ የትውልድ ወቀሳ ሳይፈሩ በግልጽ በአደባባይ እየፈፀሙ ያሉትን የወንጀል ድርጊት እናጋልጥ ብሎ መድከም ከምን የመጣ የዋኅነት ነው ?

የወያኔዎቹን ማንነትና ከወሰን ያለፈ ኢሰብዓዊነት በትክክል ሊግልጻቸው የቻለውን በሌላ የታሪክ አጋጣሚ በሚገባ የተገለጸበትን አባባል ተነግሮት ነበር የተባለው፥ የዘረኛው የናዚ ፓርቲ መሪ የነበረው አዶልፍ ሂትለር ነበር ። የተናገረውን እንጠቅሳለን።

**“ የጀርመንን ሕዝብ ደስታ እንደገና ለማምጣት ፥ ኢሰብዓዊነታችን ወሰን እንደማይኖረው በሙሉ ልብ መናገር እንችላለን። ”**

በተመሳሳይ መልኩና በዛሬው የሀገራችን የታሪክ አጋጣሚ ደግሞ ወያኔዎቹ ስብዕናቸውን ራሳቸው በሚከተለው አባባላቸው ገልጸውታል ።

<u>የትግራይን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት ስንል የተነሳንበትን ዓላማ ለመፈፀም ሰብዓዊነት የሚባል ነገር አይኖረንም። “ ለትግራይ ያልሆነች ኢትዮጵያም ትበጣጠስ ” ።</u>

ታዲያ ይህንን ያሉትን ሰዎች ማንነት በሚገባ ያላወቀ ኢትዮጵያዊ በአሁን ወቅት ይኖራል ብለን ባንገምትም፥አንዳንድ ተቃዋሚ ድርጅቶች ግን ይህንን አወቁትም አላወቁትም ወያኔን በማንነቱ ፈርጀው ለመታገል እስካሁን አልተሳካላቸውም ። ጠላቱን በሚገባ ያላወቀ ባላጋራ ደግሞ በአቸናፊነት ይወጣል ተብሎ አይታሰብም። ሕዝብንና ሀገርን ከጠላት ጥቃት ከአምባገነን ጭቆና፥እንዲሁም ከውጭ ወራሪ ኃይል ሊያድን አይችልም ። ጠላቱን ጠንቅቆ የማያወቅ ተቃዋሚም ሆነ የሀገር መሪ ለሀገርና ለሕዝብ ይጠቅማል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም ። በመሆኑም ለሀገር ማዳን ትግሉ የሚጠቅም አይደለም ። የሀገር ማዳን ትግል ሊካሄድ የሚገባወም በመላው <u>ሕዝብና በዕውነተኞቹ ተቃዋሚ ኃይሎች</u> ብቻ ነው።

ዕውነተኛ ተቀዋሚ ሲባል ቢያንስ የሚከተሉት መሠረታዊ ዕምነትና ድርጊት ሊኖረው ይገባል።

1ኛ. ወያኔ የኢትዮጵያና የዜጎቿ ጠላት መሆኑን አምኖ ጠላትን መቋቋም የሚቻልበትን ስልት ቀይሶ በቆራጥነት መታገል፥

2ኛ. ወገተኝነቱና ታማኝነቱ ለኢትዮጵያና ለዜጎቻ ብቻ መሆኑን አውቆና አሳውቆ፥ በተግባር የሚገልጽበትን ሁኔታ እያመቻቸ የኢትዮጵያን ጠላት መፋለም፥

3ኛ. ተመሳሳይ ዓላማና ግብ፥ ራዕይና ብሄራዊ አጀንዳ ያላቸው ኃይሎች በአንድ ጎራ ተሰልፈው፥ የኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ኃይል ሆኖ መገኘት፥

4ኛ. ጠላትን በሚገባ ማወቅ የትግሉን ዕድሜ የሚያሳጥረው መሆኑ ወሳኝ እንደሆነ መረዳት፥

5ኛ. ከላይ የተዘረዘሩትን አሟልተናል ብለው ከልብ የሚያምኑ ድርጅቶች ውይይት መጀመር የወቅቱ አጣዳፊ ተግባር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገራዊ ጥያቄም ጭምር መሆኑንም በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል።

ወጣም ወረድ ግን፥ ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት መሆኑን ተረድቶ ፥ጠላትን ለማጥቃት የሚያስፈልገውን ሁሉ ዝግጅት እያደረጉ ኅብረት መፍጠር ጊዜ የማይሽረው ሀቅ ነው ። ወያኔን በምርጫ እናስወግደዋለን የሚለው ምኞት ወደ ቀትር ኅልም መለወጡን እራሱ ወያኔ አረጋግጦታል ። ጠላቱን በሚገባ የማያውቅ ተቃዋሚ በአዲሱ የትግል ምዕራፍ የሚያስተናግደው አይኖርም ። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅ ጠላቱን በሚገባ ካወቀበት ደረጃ መድረሱ ብቻ ሳይሆን፥ የራሱን ውሳኔ በወሰደበት ሁኔታ ላይ በመገኘቱም ጭምር ነው ። የሕዝብን የመጨረሻ ውሳኔ ደግሞ ሊሽረው የሚችል ኃይል አይኖርም።